የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፪
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

25th Year No.62
ADDIS ABABA 25th April, 2019

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፩/፪ሺ፲፩ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግስት መካከል የተፈረመውን የኢንቨስትመንት ማስፋፋት እና ጥበቃ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ........ገጽ ፲፩ሺ፪፻፵፰

## Content

Proclamation No.1131/2019

Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the United Arab Emirates on the Promotion and Reciprocal Protection of Investment Ratification Proclamation..................................Page 11,248

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፩/፪ሺ፲፩

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግስት መካከል የተፈረመውን የኢንቨስትመንት ማስፋፋት እና ጥበቃ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግስት መካከል የተፈረመው የኢንቨስትመንት ማስፋፋት እና ጥበቃ ስምምነት ሕዳር ፳፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአቡዳቢ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፳፬ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### Proclamation No.1131/2019

### PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE UNITED ARAB EMIRATES ON THE PROMOTION AND RECIPROCAL PROTECTION OF INVESTMENT

WHEREAS, the Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the United Arab Emirates on the Promotion and Reciprocal Protection of Investment was signed in Abu Dhabi on the 3rd day of December, 2016;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 2nd day of April, 2019;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግስት መካከል የተፈረመውን የኢንቨስትመንት ማስፋፋት እና ጥበቃ ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፴፩/፪ሺ፲፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ስምምነቱ ስለመፅደቁ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መንግስት መካከል ሕዳር ፳፬ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአቡዳቢ የተፈረመው የኢንቨስትመንት ማስፋፋት እና ጥበቃ ስምምነት ፀድቋል፡፡

**፫. አስፈፃሚ አካል**

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ስምምነቱን የማስፈፀም ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፯ ቀን ፪ሺ፲፩ ዓ.ም**

**ሳህለ ወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. Short Title**

This Proclamation may be cited as "Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the United Arab Emirates on the Promotion and Reciprocal Protection of Investment Ratification Proclamation No.1131/2019".

**2. Ratification of the Agreement**

The Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the United Arab Emirates on the Promotion and Reciprocal Protection of Investment signed in Abu Dhabi on the 3rd day of December, 2016, is hereby ratified.

**3. Implementing Organ**

The Ethiopian Investment Commission is hereby empowered to implement the Agreement.

**4. Effective Date**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, on this 25th day of April, 2019.**

**SAHELE-WORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**